# የስደቱ ወላፈን በኖርዌ

ከብ.ወ

ስደት አዋራጅ ነው። ስደት መከራ ነው። ከአምባገነኖች እስርና አፈና ለመሸሽ ስደት። በፖለቲካው ዳፋ የሚላስ የሚቀመስ ሲታጣ ስደት። የሃገሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ ስደትን የየችግሮቹ መቅረፍያ አድርጎ ሲጠቀምበት ሳለ እነሆ አራት አስር ዓመታትን አስቆጥሯል። ሙሴን ሳይዙ ምድረበዳውን ማቋረጥ፣ እንደ ዳንኤል በአምበሶች ሳይደፈሩ ጫካውን መንጥሮ ማለፍ፣ እንደ ጌታችን እየሱስ ክርስቶስ በባህሩ ላይ መጓዝ፣ ወዘተ - ዛሬ አውሮፓና አሜሪካ የገቡ ወገኖቼ በሰመመን ተውጠው ብርክ ብርክ እያላቸው የሚመሰክሩት የሰቆቃ ታሪክ ነው። ታድያ ለዚህ ያልታደለው ወገኤም በበርሃው ላይ - "ውሃ - ውሃ" - እንዳለ ቀርቷል፣ አንዳንዱም የአውሬ ራት ሆኗል። ጥቂት የማይባሉም በባህሩ ላይ እስከነልጆቻቸው ሰጥመው ቀርተዋል። የብዙሃኑ በበርሃ እንጥፍ ብሎ የመቅረቱ፣ የአውሬ ሲሳይ የመሆኑና በጨው ባህር ውስጥ ወድቀው - "አድኑን አድኑን" - እያሉ ሰጥመው የመቅረታቸው ዜና - ልቡ ለስደት ለተነሳሳው ወገኔ ቁምነገርን ያዘለ የማስጠንቀቅያ ደወል አይደለም። "ከዚህስ የባሰ የለም - ስደቱ ይሻላል" - ባይ ነው ሁሉም። በየአረብ ሃገሮቹ የሚሰማው በሴቶች እህቶቻችን ላይ የሚደርሰው ሕልፈት፣ ከፎቅ ላይ መፈጥፈጡም ሆነ በቁም በፈላ ውሃ የመቀቀሉ ስቃይ፣ ጀርባን በአለንጋ የመተልተሉና ጭንን በእሳት የመጠበሱ ቅጣት የተሰዳጁን ወገኔን ቁጥር አልገደበም።

ወቅቱ የምጣኔ ሃብት መናጋትን በማስከተሉ የበለጸጉት ሃገሮች በራቸውን ጥርቅም አድርገው ለመዝጋት ባደባባይ እየመከሩ ነው። ትላንት የአዕምሮውንና የጉልበቱን ኃይል ለጥቅማቸው ሲሉ እንዳልተሻሙ ሁሉ አውሮጳውያኖቹ ዛሬ ደግሞ ስደተኞች ሃገራቸውን ለቀውላቸው እንዲወጡ እየለፈለፉ ነው። የሌሎቹ አሕጉራት ሕዝቦች ክምችት ወደፊት ማህበራዊ ቀውስን ሊያስከትል ይችላል በሚል ስጋትም አውሮጳውያን በሰበብ አስባቡ የመጤውን ቁጥር ለመቀነስ ጥረት እያደረጉ ነው።

በሕዝቦች ልማትና የሰብዓዊ መብት አያያዝ እጅግ ከፍተኛ ደረጃ ከያዙት ሐገሮች መካከል እንደ አንዷ የምትቆጠረዋ ኖርዌም ብትሆን መልስ ያላገኙ ስደተኞች ሃገሪቱን ለቀው እንዲወጡ መወትወት ከጀመረች ቆይታለች። በተለይም ደግሞ በዚሁ ዓመት መግቢያ ላይ ከወያኔው መንግስት ጋር አንድ ስምምነት ላይ ደርሳ የመኖርያ ፈቃድ ያልተሰጣቸው 700 ገደማ የሚሆኑ ስደተኞችን በፈቃደኝነት ወይም አስገድዶ ለመመለስ በዝግጅት ላይ ትገኛለች።

እንደ ጽዮን ታቦት ይስተዋሉ፣ እንደ ብራናው መጽሃፍ ይወደሱ፣ እንደ አንበሳ ይፈሩ የነበሩ ኢትዮጵያኖች ዛሬ ተንቀው - "ውጡ አንፈልጋችሁም" - እየተባሉ ነው። ቤተክርስትያንን የሙጥኝ በማድረግ ተማጸኑ። ተደጋጋሚ ሰላማዊ ሠልፎችን ጠሩ። ከከተማ ከተማ ረጅም የእግር ጉዞ አደረጉ። እንዲሁም የሕዝቡንና ባለስልጣናቱን አስተሳሰብ ይለውጡ ዘንድ በርካታ ጽሁፎችን ሳይቀር በተኑ። በሰባዓዊ መብት ተሟጋች ድርጅቶች፣ በሃገሪቱ የፖለቲካው ሰዎችና በብዙሃን መገናኛዎች ሳይቀር በየአራቱ ማእዘናት የቅስቀሳና የፕሮፖጋንዳ ትግሎች ተካሄዱ። በኖርዌ የኢትዮጵያ ኮሙኒቲም ታላቅ ግብረ ኃይል አቋቁሞ የተደራጀ እንቅስቃሴ፣ ስብሰባዎችና ውይይቶችን አድርጓል። ኖርዌ ግን ወይ ፍንክች። አስኮብላዮች ተሰዳጆችን ወደ ሃገራችን አመጡብን እኛ ደግሞ ወደ ሃገራቸው ለመመለስ

EthioLion.Com

አስኮብለዮች የሉንም በማለት ኖርዌ ምሬቷን ባደባባይ እስከመናገር ደርሳለች።

እንደው ለነገሩ ኖርዌስ - "ውጡ" - ትበል - እኚህ የአናብስት የትውልድ ሃረጎች "እንፈልጋችሁም ውጡልን" - ሲባሉ - "እረ ወድያ እኒም እኮ ሃገር አለኝ - በታሪክ የኮራች በጠላቶቿ ያልተደፈረች ሃገር" - ብለው ውልቅ ብለው መውጣት ያልቻሉት የኢትዮጵያ ልጆች ምን አባዜ ተጠናውቷቸው ነው?

ምንድነው ይሄ ሁሉ ጉድ? - የኢትዮጵያን ሕዝብ ኩራት ምን ሰበረው? - ቀብራራነቱንስ ምን ሰለበው? - "ከዚህስ ሞት ይሻላል - እንደ በላይ ዘለቀና አበበ አረጋይ አርበኞችን ተቀላቅዬ ወያኔን እፋለማለሁ" - የሚል ጀግናስ ለምን ጠፋ? ምቾቱን ለቆ መውጣቱ አላስቻለውም ወይንስ እወያኔው የዘር ፖለቲካ ውስጥ ዳግም መነከሩ አዕምሮውን አወከው? - የኖርዌ የነዳጅ ሃብት ቀልቡን ሳበው ወይንስ የወገኑ ሰቆቃና የዘረኝነቱን ግፍ ታወሰው? - የፈረንጆቹን ሥልጣኔና ሽቅርቅር ኑሮን ተላመደው ወይንስ ሲመለስ አንጋጦ የሚጠብቀው የድህነቱ ጣረሞት ወይንም እስር አስፈራው።

ምናልባት ወገኔን ሃገሩን የሚያስጠላ ድግምት በጭንቅላቱ ላይ አዙረውበት እንጂ ውጣልን እየተባለስ ልመናውን የሚደረድርበት ትእግስት አይኖረውም ያስብላል ነገሩ። ማንስ ቢሆን ከሰው ቤት ምቾት ይልቅ ባላገርነቱ ሳይበልጥበት ይቀራል? - የሰው ሃብትስ ቢሆን ከወገኑ ፍቅርና የሃገር ሽታ ይበልጣልን? - የፈረንጆቹስ ሽቅርቅር ኑሮና ሥልጣኔ ለኢትዮጵያውያኑ ምኑ ነው? ጥቂቱ ተላላስ እሺ - ምናልባት ምቾቱ፣ ገንዘቡና ሽቅርቅር ኑሮው ደልሎት ይሆናል - ብዙሃን ኢትዮጵያውያን ግን የሰው ሃገር ኃብት የሚናፍቅ ባህልን አልተለማመዱም። ብዙሃኑ ስደተኛ አልመለስም ያለበት አንድ ሁነኛ ምክንያት ግን ይኖራል ።

ስደት በንጉሱ ዘመን ነበር። ሃገሬ ኢትዮጵያ በፋሺስት እጣልያ አገዛዝ ሥር ወድቃ ከማይ ስደት ያዋርደኝ ብሎ ለአምስቱ ዓመታት በኬንያ፣ ሱዳን፣ እረየሩሳሌምና እንግሊዝ የቆየው ስደተኛ ሃገር ነጻ ስትወጣ ተመልሷል። የደርግ ቀይ ሽብርን፣ እስርን ብሔራዊ ውትድርናን በመፍራት የሚሰደደው ብዙ በሆነበት ወቅት እንኳን ትምህርቱን ወይንም የሥራ ጉብኝቱን ጨርሶ የሚመለሰው ኢትዮጵያዊ ቁጥር ቀላል አልነበረም። በደርግ ዘመን ብዙ አሳርና ፈተና ደርሶበት ሳለ ሃገሬን ትቼ አልሰደድም ያለው ወገኔ ቁጥርም ብዙ ነበር። ዛሬ ግን እንዴት እንደሚወጣ መላው የተሳካለት ሁሉ እንዴት እንደሚመለስ ግን ውሉ ጠፍቶበታል። ምንድነው ሚስጥሩ - ኢትዮጵያ ሃገሬ አበቃላት እንዴ?

ዛሬ የመብቶች መሸራረፍ ብቻ ሳይሆን ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነት እየተሸረሸሩ ነው። ቀድሞ ኢትዮጵያን በጸሎታቸው ትጋት ይማጸኑላት የነበሩት ጠንካራ የእስልምናና የክርስትና እምነት ተከታዮችም ሳይቀር በወያኔው አዚም ተዳክመዋል። ፓትርያርኩ ለዳንኪረኛዋ የክብር አቀባበል እስኪያደርጉ ድረስ በእግዚአብሄር አሹፈዋል። የሃገሪቱ ጳጳሳት በመለኮታዊ አማናዊነታቸው ትንግርት እንዳልተባሉ ሁሉ ዛሬ ግን ለኢትዮጵያ ህልውና የሚቆሙ ደፋሮችን ማነሳሳቱን ወስለታውን ማውገዙን ዘነጉት። ኢትዮጵያዊነት ራሱ እምነት ሆኖ ሳለ - "ኢትዮጵያዊ ነኝ" - ማለት እፍረት እስከመሆን ተደረሰ። "እናንት የእስራኤል ልጆች ለኔ እንደ ኢትዮጵያውያን አይደላችሁምን?" - ተብሎ በመጽሃፍ ቅዱስ የተጻፈው መለኮተ ምስጢር ተዘንግቶ ዜግነትን መለወጥ ሳይቀር ስልጣኔ እስከመሆን በቃ።

የወያኔው የልማቱ የሰበካ ወሬ ለራበው ወገኔ ጣር ነው። የነጻነቱ መንሸርሸርና በችግር መጠበሱ ተጨምሮ

ኢትዮጵያዊነትን እስከሚያስጠላ ድረስ ወያኔ የቀመመው የዘረኝነቱ ፖለቲካ መርዝ የመሰደዱ ዋነና ምክንያት ሆኗል። መደኽየቱ፣ መራቡና መፈናቀሉም ያሰድዳል። አዎ - ለስደቱ የዳረገው የነጻነቱ እጦትና የፍትህ መጓደል - እንዲሁም ስደቱ ያተረፈለት የማንነቱ ቀውስ ተዳምረው ነው ወገኔን በኩራት ወደ ሃገሩ እንዳይመለስ ያገዱት። በእርግጥም ምቾቱና ንዋዩ ጥቂቱን ቢያማልልም እንኳን - ኢትዮጵያዊነት ተረጋግጦ ኅጠኝነቱ ተወግዶ ቢሆን ኖሮ - አብዛኛው ስደቱን ረግጦ በነቂስ ይመለስ ነበር። ኢትዮጵያዊ በቅንጦትና በንዋይ ተታልሎና አይኑን በጨው አጥቦ የሃገሩን አፈር ዳግም ላለማየት የሚያስችል ልቦና ይኖረዋል የሚል ግምት ጨርሶ አይኖርም።

በኖርዌ/በዓለም የሚገኘው ኢትዮጵያዊ ስደተኛ ከግራና ቀኝ በሚነፍሱት ወላፈኖች ሊጠበስ ነው። አንደኛ - የኢትዮጵያ ታሪክና አልበገሬነቷ ዘወትር የሚከነክናቸው አውሮጳውያን የኢትዮጵያውያኑን ማንነት ሊወጉ የሚችሉት ማንኛውም ዓይነት ፍላጻን ከመወርወር ወደ ኋላ አይሉም። ዛሬ "ውጡልን" ብለዋል ነገም ሌላ ፍላጻ ይወረውራሉ። ራሳችኑ በማወቅም ይሁን ባለማወቅ ለካርድዋ ስንል የተናዘዝናቸው ገበናዎቻችን ነገ መቶ ፍላጻዎች ሆነው ራሳችንኑ ይወጉናል። ሁለተኛ - በሃገራችን እንደመንግስትነት የመግዛት እድሉን ያገኘው ወያኔም ማሰደዱንም ያውቅበታል። ቆይቶም የውጭውን ተቃዋሚ አንገት የሚያስደፋበትን ማንኛውን ተንኮል ከፈረንጆቹ ጋር በመመካከር ያውጠነጥናል፣ ለተግባራዊነቱም ይንቀሳቀሳል። "ኑ - ተመለሱና በነጻነቱ እጦት፣ በዋጋው ግሽበትና በሕዳሴው ፕሮፖጋንዳ ተጠበሱ" - እያለ ነው። አቶ መለስን ክፉኛ ያወገዙት የኖርዌ ስደተኞች ከቀኝም ከግራም በሚነፍስ ወላፈን ማህል ይገኛሉ። አንዳንዱ ሃገሩ ቢመለስ መከራ ይጠብቀዋል - ባለመመለሱ ጸንቶ እመጠለያው ካምፕ ቢቆይም ከእጅ ወደ አፍ ኑሮው ያስመርረዋል።

ኖርዌ እንደማንኛውም ሉዓላዊ ሃገር ጥቅሟን ለማስጠበቅ ከኢትዮጵያው መንግስት ተብየው ጋር ስትፈራረም መልስ ለተነፈጉት ስደተኞች እጅግ ድንጋጤ፣ ፍርሃትና ውርደት ነበር። "ውጡ - አንወጣም" - የኢትዮጵያውያኑን አበሳ አበዛ እንጂ ከአባቶች የተወረሰውን ሃሞተ ኮስታራነትን አልቀሰቀሰም። በዚሁ - "ውጡ አንወጣም" - አታካራ ውስጥ የተዋረደው በመላ ዓለም ላይ ተበትኖ የሚገኘው ኢትዮጵያዊው ስደተኛ ነው። ለነገሩስ - "እሺ ተቀመጡ" - ቢባልስ ከዚህ በኋላ ያለው የሰው ቤት እንጀራ በኩራት ይበላልን። በዓለም ላይ የተበተንህ ኢትዮጵያዊ ሁሉ ይህን ልታስተውል ይገባሃል። ስደትን ማስወገድ እንጂ ስደትን ምርጫ ማድረግ ለኢትዮጵያውያኑ የአሳር እንጀራ እንጂ የበረከት ጽዋ ሲሆን አልታየም። ስደትን ለማስወገድ በኢትዮጵያ የተንሰራፋውን አምባገነንነትንና ዘረኝነትን በቁርጠኝነት መዋጋት ያስፈልጋል።

እግዚአብሄር ሆይ በዓለም የተበተኑትን የኢትዮጵያ ልጆች ወደ ሃገራችው ይመለሱ ዘንድ ዳግም ሙሴን ታስነሳ ዘንድ እንለምንሃለን - አሜን።

አስተያየትዎን በ - bisrat.smart@yahoo.com - ላኩልኝ።